በአቤል ተጀምሮ የሞት ፅዋ መቅመስ፣
የሰው ልጅ ይሞታል እስከ ዛሬ ድረስ።
የማይቀር መሆኑን ፍጥረት እያወቀው፣
ሞት አይለመድም ሁልጊዜ እንግዳ ነው።
ክርስቶስ የአንተ ልጅ ተለይቶን ከእኛ፣
ጥሪ ደርሶት መጥቷል የዛሬ ተረኛ፥
ከቅዱሳኑ ጋር በገነት አኑረው፣
ነጩን ልብስ አልብሰህ ከፊትህ አቁመው፥
ሥርግወ-ሥላሴ አባት መልካም ልጅህ፣
ግርማ-ሞገስ ሁነው እንዳይወጣ ከእጅህ።
        የክህነት ምስጢር ለአሮን የሰጠኸው፣
        አብርሃምን መርጠህ ዘሩን ያባዛኸው፣
        ሙሴን ለፈርዖን አምላክ ያደረከው፣
        ሳሙኤልን ጠርተህ ሌሊት ያናገርከው፣
        ዐልዐዛርን ከሞት ቀስቅሰህ የጠራህ፣
        በምድረ-በዳው ላይ ዩሴፍን የመራህ፣
        ሥርግወ-ሥላሴን በዕረፍት ውኃ ምራው፣
        ከቅዱሳንህ ጋር ለመንግሥትህ አብቃው፥
        በሚያልፈው ርስት ድርሻ ሰጠው ቦታ፣
        ይኼን ሀላፊ ዓለም ትቶት መጥቷል ጌታ
        የአባቴ ቡሩካን ብለህ ስትጣራ፣
        በቀኝህ አቁመው ከነአብርሃም ጋራ።
ተኝቶ መባነን ልምዱ እንዳልነበረ፣
ምነው ዛሬስ ሥርግው ጋደም ብሎ ቀረ፥
ተመችቶት ነው ወይ ምናልባት አፈሩ፣
ይኼን ያህል ጊዜ ሳይባንን መኖሩ፥
እስኪ ምን አገኘህ ምን ተማርክ አንተ ምድር፣
፵ ቀን ሙሉ ምሁር ስታሳድር።
የማይተካ ሰው ስመ ጥሩ ሞተ፣
ሙኒክ አደባባይ ጨኸት በረከተ፥
የማይቀር ሆነና ሞት በሰው መድረሱ፣
ሥርግወ-ሥላሴን ተለየችው ነፍሱ፥
ሰው መርጠህ ብታስቀር ሞት በየዘመኑ፣
አይሞትም ነበር ሥርግው ደርሶ ቀኑ።
        ዕውነት አልፈኻል ወደ አንተ ሰው ጨክነህ፣
        ናፋቂ ቤተሰብ ወዳጅ ዘመድ ትተህ።
        ዕንግዳ ምስጢር ነው ዛሬስ የገጠመን፣
        ይኼን ዕንቆቅልሽ ማን ፈቶ ይንገረን።
አልሞትክም እንዳንል እስትንፋስ የለህም፣
ሞተኻል እንዳንል ታሪክህ አይሞትም፥
ግራ ገብቶን አለ የአባባል መንገዱ፣
“አለ” ወይም “የለም” ብሎ ለመፍረዱ፥
የማይሞተው ሥራህ ሕያው ሆኖ ስናይ፣
እንዴት ሞተ እንበል ጥሪ ደርሶት ከላይ።

በንጉሥ ሰሎሞን በጠቢብ አባባል፣
እግዚአብሔር በሰጠው በተመረጠው ቃል፡
“ከመልካም መዐዛ መልካም ስም ይበልጣል”
ሥራህ ደግነትህ ሲታወስ የኖራል።
ዘግበህ ያስቀመጥክ ታሪክ እንዳይጠፋ፣
ላለው ለሚተካው ለትውልዱ ተስፋ፡
ሥራህ ሕያው ሆኖ ዝንተ-ዓለም ሲዘከር፣
በአገር በውጭ አገር ታሪክህ ሲነገር፡
አንተ ብቻ ጠፋህ ከዕውቀት አደባባይ፣
እንደ ቀድሞ ገድልህ ገና ብዙ ሳናይ፡
ለማን ትተህ አለፍክ የታሪክ አደራ፣
ሥርግው አገኘህ ወይ እንዳንተ የሚሠራ?
ለመልካሙ ግብርህ ለፈፀምከው ሙያ፣
ምልክት ቀመልህ ለስምህ መጠሪያ
ሥርግው ብትሞትም ብሥራህ ሕያው ነህ፣
በእያንዳንዳችን ልብ የቁም ኃውልት አለህ፡
ዘግበህ ለማለፍ የታሪክ አደራ፣
ሜዳና ቁልቁለት ዳገትና ጋራ፣
ወጥተኻል ወርደኻል ደክመኻል በብዙ፣
እማኝ ምሥክር ነው ተራራና ወንዙ
ሚዛን አይመዝነው መሥፈሪያም አይሰፍረው፣
ለትውልድ ይተርፋል ትናንት የሠራኸው፡
በፈረስ በበቅሎ በአጋሰስ ተጠቅመህ፣
በኢትዮጵያ ገዳማት በየዋሻው ዞረህ
መጻሕፍቱን ብታይ ተቀደው ተቃጥለው፣
ታሪክ አልባ እንዳንሆን ታሪክ እንደሌለው፣
ዕርዳታ ጠይቀህ ገንዘብ አሰባስበህ፣
ታሪክ እንዳይጠፋ በፊልም አስቀርፀህ፡
ለዕድሜ ልክ የሚሆን እኩራ ድል ፈፅመህ፣
ከዚች ምድር አለፍክ ቋሚ ታሪክ ሠርተህ፡

በኢዮብ ይመስላል አንተ ሰው ትዕግስትህ፣
በአቤል ይመስላል ፍፁም ደግነትህ፡
በሌላው በቀረው ሥርግው አንተነትህ፣
ትመስል ኤልያስ በብቸኝነትህ፡
ከወላጅህ ወርሰህ ዕምነት ሃይማኖትን፣
በሞቱ ሳትመስለው ቀረህ አባትህን፡
ሐብለ-ሥላሴማ ባደገበት ሞተ፣
እንደ-ወጡ መቅረት ከማን ተማርክ አንተ፡
ያስተማርከው ምሁር ያስተማርከው አገር፣
አፈር ለመመለስ አልቅሶ ለመቅበር፡
ሳይሆንለት ቀረ ዕድሉ ሳይገጥመው፣
እንደወጣህ ቀርተህ ሥርግውን ያህል ሰው፡

*ቅኔ ሥላሤውን - ቅኔ መውድሱን፣*
*ቅኔ ዘይዕዜ - ቅኔ ሚ - በዝኀን፡*
*ቅኔ ዘአምላኪየ - ቅኔ ዋዜማውን፣*
*ዛሬ ማን ይቀኘው ጉባዔ ቃናውን*
*ከቅኔው መካከል ሥርግው ከቆጠርከው፣*
*ቅኔ ዘአምላኪየን በተግባር ፈፀምከው፡*
*ወደ አምላክህ ተጓዝክ ለዘላለም ኑሮ፣*
*በምድር ያደረግከው ቅን ሥራህ ተቆጥሮ።*

እንግዲህ ደህና ሁን ሥርግወ-ሥላሴ!
ሰላምታ አድርስልን ለሐብለ-ሥላሴ፡
በነአብረሃም ዕቅፍ እግዚአብሔር ያኑርህ፣
የያዕቆብ አምላክ ይታደግ ያስብህ።

አቶ በትረ ገብረ ዮሐንስ
ሚኒያፖሊስ
ሚኒሶታ